## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 544/2013

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያ ቁጥር 537/2013ን /እንደተሻሻለው/ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 551/1999 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 544/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ማሻሻያ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያ ቁጥር 537/2013 /እንደተሻሻለው/ እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የመመሪያው ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡፡

1. የምርት ገበያው በምርት ገበያው ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ወይም በደንቡ የጊዜ ገደብ ላልተወሰነላቸው ጉዳዮች በህሊና ግምት በቂ በሚባል ጊዜ ውስጥ የዲስፒሊን እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ባለስልጣኑ የምርት ገበያው ጉዳዩን መርምሮ እርምጃ በመውሰድ ወይም የተፈፀመ የህግ ጥሰት አለማግኘቱን በማረጋገጥ እንዲያሳውቀው በጽሁፍ ትዕዛዝ ሊሰጥ ወይም የራሱን ምርመራ አካሂዶ ማንኛውንም የምርት ገበያ አባል ሊያግድ፣ ከአባልነት ሊያስወግድ ወይም አግባብነት ያለው ሌላ የዲስፒሊን እርምጃ ሊወስድ ወይም ማንኛውም ሰው በምርት ገበያው እንዳይሳተፍ ሊከለክል ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተው እርምጃ የሚወሰደው በምርት ገበያው ደንቦች መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

2. የመመሪያው ክፍል ስድስት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 /ለ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ተተክቷል።

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተውን ያላሟላ ወይም መመዘኛዎቹን ስለማሟላቱ ማረጋገጥ ያልቻለ አባል በምርት ገበያው ደንብ መሠረት የደንበኛን ሂሳብ ማዛወር፣ እንደዚሁም መመዘኛዎቹን ማሟላቱን

እስከሚያስረዳ ድረስ እንደ አባል የንግድ እንቅስቃሴ ማድረግን ወዲያውኑ ማቆም እና ይህንኑ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። በመፍረስ ላይ ያለ ድርጅት ቀሪ ሥራን ለማጠናቀቅ ሲባል በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲሰራ በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በስተቀር በምርት ገበያው የንግድ ስራ መስራት አይችልም። በተጨማሪ አባሉ መመዘኛዎቹን ሊያሟላ የሚያስችለው ችሎታ እንዳለው ባለስልጣኑን በሚያሳምን ሁኔታ ያረጋገጠ ከሆነ ባለስልጣኑ አባሉ የደንበኛን ሂሳብ ሳያዛውር እንዲሁም ከላይ በተቀመጠው መሠረት የንግድ ሥራውን መሥራት ሳያቆም ለ30 የሥራ ቀናት እንዲቆይ ማድረግ ይችላል። የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን መመዘኛዎች ባላሟላ አባል ላይ ሊወሰድ የሚችለውን እርምጃ እንደሚከለክል ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም።

3. የመመሪያው ክፍል ስድስት አንቀጽ 11 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 11 ተተክቷል።

11. እውቅናን ስለማሳደስ

1. እውቅናው እንዲታደስለት የሚፈልግ ማንኛውም ግብይት ፈፃሚ በየሶስት ዓመቱ ፀንቶ የሚገኘው የእውቅና ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ቀጥሎ ባሉት አራት ወራት ውስጥ አስፈላጊውን መመዘኛ በማሟላት እና የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የእውቅና እድሳት ማመልከቻ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡ ፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የእውቅና እድሳት ማመልከቻ ያላቀረበ ግብይት ፈፃሚ በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በስተቀር በምርት ገበያው የሚያደርገውን የግብይት ስራ ወዲያውኑ በማቆም ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር እና ከአንድ ወር ላነሰ ጊዜ ብር 2,000 /ሁለት ሺህ ብር/ ቅጣት በመክፈልና አስፈላጊውን መመዘኛ በማሟላት በቀጣዮቹ ሁለት ወራት ውስጥ የእድሳት ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተወሰነው ጊዜ ካለፈ በኋላ የእውቅና እድሳት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ግብይት ፈፃሚ የዘገየው ከቁጥጥሩ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች መሆኑን አስረድቶ በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ማመልከቻው ተቀባይነት አይኖረውም።

4. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሠረት እውቅናው ካልታደሰ ወይም እውቅናውን ለማሳደስ ካልፈለገ

በምርት ገበያው ያለውን የአባልነት መቀመጫ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡ የአባልነት መቀመጫ የሚተላለፍበት ዝርዝር ሥነ ሥርዓት አግባብነት ያላቸውን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንቦች የተከተለ ይሆናል፡፡

4. የመመሪያው ክፍል ሰባት አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 7 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

7/ የደንበኛውን ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ደንበኛው መገበያያ ወይም ከተቀማጭ ሂሳቡ አላማ ውጭ እና ከተቀማጩ ሂሳብ ከፋይ የሆነው ደንበኛ ከተቀማጩና ከክፍያው ጋር በተያያዘ ከሚያደርጋቸው ግብይቶች ውጭ መጠቀም ወይም መክፈል፤

5. የመመሪያው ክፍል ሰባት አንቀጽ 7 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

7. ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ በደንበኛው የምርት ገበያ የባንክ ሂሳብ ላይ ከተቀማጭ ሂሳቡ አላማ ውጭ የማዘዝ ስልጣን የለውም፡፡ ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ የደንበኛውን ሂሳቦች ለይቶ መያዝ አለበት፡፡

6. የመመሪያው ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ተተክቷል፡፡

ለ/ የሕግ ጥሰት ስለመኖሩ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን የሕግ አስከባሪው ዳይሬክተር በዚሁ ክፍል አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ይሁንታ ሲያገኝ ጉዳዩ ለአስተዳደራዊ ችሎት ቀርቦ ይታይ ዘንድ ባለስልጣኑን በመወከል ክስ እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡

7. በመመሪያው ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 10 ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተጨምሯል፡፡

3. ባለስልጣኑ የሕግ ጥሰት የተፈፀመ መሆኑን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የሕግ ጥሰቱ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመታት ውስጥ ለአስተዳደራዊ ችሎቱ ክስ ካላቀረበ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

8. የመመሪያው ክፍል አስር አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡

3/ ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ካልሰጠ የአስተዳደር ችሎቱ የቀረበለትን ክስና ማስረጃ ከህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

9. የመመሪያው ክፍል አስር አንቀጽ 16 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 16 ተተክቷል፡፡

16. ክስን ስለማንሳት

የሕግ አስከባሪው ዳይሬክተር ከባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ጋር ከተማከረ በኋላ አስተዳደራዊ ችሎቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ በርሱ ፊርማ የተረጋገጠ የጽሁፍ ማመልከቻ በማቅረብ ወይም በህግ አስከባሪው ባልደረባ በኩል እንዲቀርብ በማድረግ ክሱን ሊያነሳ ይችላል፡፡

10. የመመሪያው ክፍል አስራ አንድ አንቀጽ 2 የመግቢያ ዓረፍተ ነገር እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

2. ባለስልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000/ አምስት ሺህ/ ያላነሰ እና ከብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ያልበለጠ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡

11. የመመሪያው ክፍል አስራ አንድ አንቀጽ 3/ሀ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ ተተክቷል፡፡

ሀ/. የምርት ገበያውን በተመለከተ ከጥሰቱ ክብደት እና መጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000 /አምስት ሺህ/ ያላነሰና ከብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ

ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከ750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ያልበለጠ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡
፡

12. የመመሪያው ክፍል አስራ አንድ አንቀጽ 4/ሀ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ ተተክቷል።

ሀ. የክፍያ መፈፀሚያ ተቋማትን በተመለከተ ከጥሰቱ ክብደትና መጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000 /አምስት ሺህ ብር/ ያላነሰና ከብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/

ያልበለጠ፣ ሆኖም በድምሩ ከ750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ያልበለጠ ቅጣት ሊጥል ይችላል።

13. የመመሪያው ክፍል አስራ አንድ አንቀጽ 5/ሀ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ ተተክቷል።

ሀ/ የግብይት ፈፃሚን በተመለከተ ከጥሰቱ ክብደት እና መጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000 /አምስት ሺህ/ ያላነሰና ከብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከ500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ያልበለጠ ቅጣት ሊጥል ይችላል።

3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ ከፀደቀበት ከዛሬ የካቲት 01 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ